የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፣ ቅፅ 12 ቁጥር 8 የካቲት 1998

# ዜና አመዝኤ



## በዚህ እትም ውስጥ


ለየካቲት ወር ከ366 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል
ገጽ 3

በቦረና ዞን የተከሰተው የዝናብ እጥረት ያስከተለውን ድርቅ ለመከላከል ጥረት እየተደረገ ነው
ገጽ 3

ኬር ቦረና በ21 ሚሊዮን ብር በጀት በአደጋ ተጋላጭነት ቅነሳ ፣ በምግብ ዋስትናና በጤና ክብካቤ ላይ ያተኮሩ ኘሮጀክቶችን እያካሄደ ነው
ገጽ 5

በሶማሌ ክልልና ቦረና ዞን በተከሰተው ድርቅ ዙሪያ ከለጋሾችና መንግሥሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ውይይት ተካሄደ
ገጽ 5

ከሁለት ማዕከላዊ መጋዘናት ከ416 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተሠራጨ
ገጽ 7


# በሶማሌ ክልልና ቦረና ዞን የተከሰተውን የድርቅ አደጋ ለመቋቋም አስፈላጊው እርምጃ በመወሰድ ላይ ይገኛል

በሶማሌ ክልል እና በኦሮሚያ ቦረና ዞን በጥቅምትና ህዳር ወራት በቂ ዝናብ ባለመዝነቡ የተከሰተው የውሃና የግጦሽ እጥረት በእንስሳት ላይ ከፍተኛ ችግር ከማስከተሉም በላይ በሶማሌ ክልል በዘጠቃ ዞኖች 1 ሚሊዮን 535 ሺህ 148 ፣ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን 155 ሺህ ህዝብ ተጎጂ ሆኗል:: በሶማሌ ክልል አፍዴር፣ ሊበንና ጎዴ፣ በኦሮሚያ ቦረና ችግሩ ይበልጥ አይሎባቸው የሚገኙ ዞኖች ናቸው:: ከአጎራባች ኬኒያና ሶማሌ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ እንስሳት ግጦሽ እና ውሀ ፍለጋ ድምበር ዘልቀው መፍለሳቸው ችግሩን ይበልጥ አባብሶታል:: የተከሰተውን ችግር ለመቋቋም የምግብ ዕደላና ሥርጭት ፣ የሰውና የእንስሳት ጤና የሚከታተሉና የሚያስተባብሩ ከአመዝኤ ፣ ከጤና ጥበቃ ፣ ግብርና ሚኒስቴር እና ከውሀ ሀብት ባለሥልጣን የተውጣጡ ባለሙያዎች ችግሩ ወደተከሰተባቸው አካባቢዎች በመዘዋወር በሚያቀርቧቸው አስፈላጊ መረጃዎች መሠረት እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ከዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈጻጸምና ክትትል መምሪያ የተገኘ መረጃ ያመለክታል::



በዚሁ መሠረት ለሶማሌ ክልል ለጥር ወር 1998 ከተመደበው 290 ሺህ 551 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ወስጥ 95 በመቶው ፣ ለኦሮሚያ ቦረና ዞን የተመደበው 28,790 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ተጓጉዞ ለተረጂዎች በመከፋፈል ላይ ይገኛል:: እንዲሁም ለሱማሌ ክልል ለየካቲት ወር ከተመደበው 281 ሺህ 267 ኩንታል እህል ውስጥ 2 በመቶ እና ኦሮሚያ ቦረና ዞን ለየካቲት ወር ከተመደበው የምግብ 25,009 ኩንታል ዕርዳታ ውስጥ 95 በመቶ በመጓጓዝ ላይ የሚገኝ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ::

የውሀ አቅርቦትን በተመለከተም በአመዝኤ ፣ ችግሩ በተከሰተባቸው ክልሎች መንግሥታትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት በሱማሌ ክልል ከ65 በላይ በኦሮሚያ ቦረና ዞን 14 ቦቴዎች ተመድበው የውሃ እጥረት በተከሰተባቸው አካባቢዎች የውሀ ዕደላ በማከናወን ላይ


በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 529259
529262
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣www.dppc.gov.et


ዜና አመዝኮ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና ተባባሪዋቹን የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዋችንና ሴሎች ተጎዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው



የውሀ አቅርቦትን በተመለከተም በአመዝኤ ፣ ችግሩ በተከሰተባቸው ክልሎች መንግሥታትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት በሱማሌ ክልል ከ65 በላይ በኦሮሚያ ቦረና ዞን 14 ቦቴዎች ተመድበው የውሃ እጥረት በተከሰተባቸው አካባቢዎች የውሀ ዕደላ በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ሌላ ዩኒሴፍ 60 የውሀ ማጠራቀሚያዎችን በሶማሌ ክልል ለሚገኙ 5 /አምስት/ ወረዳዎች ለማከፋፈል በዝግጅት ላይ የሚገኝ መሆኑንና ይኸው ድርጅት አራት የውሀ ማጠራቀሚያ ዩኒቶችንና 480 ሊትር ክሎሪን በሌሎች ሁለት ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በኩል በማቅረብ ተጎጂዎቹ የንፁህ ውሀ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በድርቁ ተጎጂ በሆኑት አካባቢዎች ያለውን ሕዝብ ጤና ለመንከባከብም በሶማሌ ክልል ክልሉ እያደረገ ካለው ጥረት በተጨማሪ የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እያንዳንዱ 3 የጤና ባለሙያዎችን ያካተተ 11 ቡድን ወደ 11 ወረዳዎች አሰማርቷል፡፡ በቀጣይም 14 ቡድኖች ወደ14 ወረዳዎች የሚንቀሳቀሱ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተመድ ህፃናት መርጃ ድርጅት /ዩኒሴፍ/ 16 የጤና ባለሙያዎችን ወደ ክልሉ ለማሠማራት በዝግጅት ላይ መሆኑም የጤና ግብረኃይል ሪፖርት አመልክቷል፡፡ የህፃናትን ጤንነት ለመንከባከብ የድርቁ ሁኔታ አሳሳቢ በሆነባቸውና ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ በታማነባቸው 21 ወረዳዎች ለ159 ሺ ህፃናት የቫይታሚን ኤ እደላ ፣ ለ137 ሺ ህፃናት ከጥገኛ ትላትሎች ነፃ ማድረጊያ ህክምና ፣ ለ187 ሺ ህፃናት የፖሊዮ ክትባት ተሰጥቷል፡፡

በሶማሌ ክልልና በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ከድርቁ ጋር በተያያዘ በእንስሳት ላይ የተከሰተውን የጤና ችግር ለመከላከል መንግሥት ፣ የተመድ አካላትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለ1 ሚሊዮን 519 ሺ 249 እንስሳት የህክምና አገልግሎት እና የክትባት ዘመቻ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ የህክምና አገልግሎትና ክትባት ከሚሰጣቸው እንስሳት ውስጥ 1 ሚሊዮን 358 ሺህ 662 በሶማሌ ክልል ፣ ቀሪዎቹ 159 ሺህ 587 ደግሞ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን የሚገኙ መሆኑንም ከግብርና ግብረኃይል የተገኘው መረጃ አመልክቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ በሶማሌ ክልል በምሥራቅ ኤሚ ለ20 ሺህ እንስሳት ፣ አሜሪካን ሂውማኒቴሪያን ኤይድ የተባለ ድርጅት ደግሞ በአፍዴር ዞን ጨረቲ ወረዳ ከአሜሪካን ህፃናት መርጃ ድርጅት በተገኘ ሥራ ማስኬጃ በጠቅላላው ለ46 ሺህ 003 እንስሳት የክትባት የህክምና አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡

በተመሳሳይ ክልሉ በአምስት ቡድኖች 70 ያህል ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪዎችን በማሰማራት በደገሀቡር ፣ ፊቅ ፣ ጎዴ ዋርዴርና ሽኒሌ ዞኖች ውስጥ በሚገኙ 11 ወረዳዎች ለአንድ ወር ያህል 500 ሺህ ለሚሆኑ እንስሳት የጤና አገልግሎት ለመስጠት በዘመቻ ተንቀሳቅሷል፡፡

የዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት ከግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ፣ ከአሜሪካን ህፃናት አድን ድርጅት እና ከሱማሌ ክልል ግብርና ቢሮ ጋር በመተባበር በሊበን ዞን ለ477 ሺ 907 እንስሳት ፣ በአፍዴር ዞን ለ325 ሺ 742 እንስሳት በጠቅላላው ለ803 ሺ 649 እንስሳት የጤና አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደሚገኝ ከግብርና ግብረኃይል የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ለዚሁ የእንስሳት ህክምና ተግባር የዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት 318 ሺ ዶላር ፣ የአሜሪካን የህፃናት አድን ድርጅት 90 ሺ ብር መመደባቸውና ለዚሁ ተግባርም የፌዴራል ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴርና የክልሉ የእንስሳት ፣ ሰብልና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ በቅንጅት 8 ቡድኖች ማሠማራታቸው ታውቋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት 110 ሺ የአሜሪካን ዶላር በመመደብ ከኦሮሚያ አርብቶ አደር አካባቢ ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን ለ159 ሺ 587 እንስሳት የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ የእንስሳት መኖ አቅርቦትን በተመለከተም ኬር ኢትዮጵያ ፣ ጉሚጋዩ እና ኢኒሼቴቭ ፎር

ከመዝኬ

ደቮሎኘመንት የተባሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከ23 ሺ በላይ ድርቆሽ ገዝተው ለቦረና ዞን በማቅረብ ላይ ናቸው። ድርቁ በእንስሳት ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለመቋቋምና የአርብቶ አደሩን ጥሪት ለመጠበቅ እንዲቻልም በኦሮሚያ አርብቶ አደር ልማት ኮሚሽን አስተባባሪነት ከአሜሪካን የሕፃናት አድን ድርጅት **(SC-USA)** በተገኘ የበጀት ድጋፍ 10 ሺህ እንስሳት ለገበያ እንዲቀርቡ ተደርጓል። በቀጣይም ተመሳሳይ እንቅስቃሴ በተጠናከረ መልኩ የሚካሄድበት ስልት መቀየሱን ለመረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ በፌዴራል ደረጃ እና በሶማሌ ክልልና በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን ወረዳዎች ድረስ በተቋቋሙ ግብረኃይሎች አማካይነት የመንግሥት መ/ቤቶችን ፣ ዓለም አቀፍና ለጋሽ አካላትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በአጋርነት እንዲሰለፉ በማነሳሳትና ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት ድርቁ በማስከተል ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለመቋቋም የተቀናጀ ሥራ በማካሄድ ላይ ይገኛል።

## ለየካቲት ወር ከ366 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል

በተለያዩ ክልሎች የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ለየካቲት ወር 1998 ዓ.ም የሚሆን በጠቅላላው 366 ሺህ 948.1 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተመድቧል።

ከዚሁ ለወሩ ከተመደበው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 333 ሺህ 234 ኩንታል በአመዝኤ ቀሪው 33 ሺህ 714.1 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተመደበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ለየክልሎቹ የሚደረገው የዕርዳታ አመዳደብም በየክልሉ ከሚገኘው ችግር ስፋትና ጥልቀት አኳያ የሚለያይ ነው። በዚሁ መሠረት ለየካቲት ወር ከተመደበው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 281 ሺህ 267.2 ኩንታል ለሱማሌ ፣ 58 ሺህ 274.1 ኩንታል ለኦሮሚያ ፣ 8 ሺህ 598.5 ኩንታል ለአፋር፣ 7 ሺህ 530 ኩንታል ለጋምቤላ ፣ 5ሺህ 817.9 ኩንታል ለደቡብ ህዝቦች ፣ 4 ሺህ 750 ኩንታል ለአማራ እና 710 ኩንታል ለቤንሻንጉል የተመደበ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

## በቦረና ዞን የተከሰተው የዝናብ እጥረት ያስከተለውን ድርቅ ለመከላከል ጥረት እየተደረገ ነው

በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን በክረምትና በበልግ ዝናብ እጥረት ሳቢያ የተከሰተውን ድርቅ ለመከላከል መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ መሆኑን የአካባቢው የመስተዳድር አካላት ገለጹ።

አቶ አብዱልቃድር አብዲ የቦረና ዞን ዋና አስተዳዳሪ እንደገለጹት በአካባቢው አጠራር “ ገና “ ተብሎ የሚጠራው የክረምት ዝናብ ባለፈው ዓመት ወቅቱን ጠብቆ ባለመዝነቡና ሥርጭቱም የተዛባ በመሆኑ በዚህ ዓመት ሲጠበቅ የነበረው የበልግ ወይም “ ሀገያ “ ዝናብ ከያቤሎና ከአሬሮ ወረዳዎች ውጪ በተቀሩት ስድስት ወረዳዎች ባለመዝነቡ የውሀና የግጦሽ እጥረት ተከስቷል። ድርቁን በተቀናጀ እንቅስቃሴ ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት ለማስተባበር ከዞኑና ከወረዳዎች የሚመለከታቸውን አካላት በአባልነት ያካተተ ኮሚቴ እንደተቋቋመ አመልክተው በፌዴራል አመዝኤ በኩልም ለ155 ሺህ ተረጂዎች የምግብ

በእንስሳት ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ለመከላከል መንግሥት እያደረገ ያለውን ጥረት ለማገዝ 5 ሺህ የርቢ ላሞችን በመመገብ ሕይወታቸውን ለማትረፍ የሚያስችል 20 ሺህ እስር ድርቆሽ ሳር ገዝቶ በማከፋፈል ላይ ይገኛል፡፡

እርዳታ ተመድቦ መከፋፈሉን ገልጸዋል፡፡

በያዝነው የአውሮጠውያን ዓመት በዞኑ ለ155 ሺህ ሕዝብ የፌዴራል አመዝኤ በጥር ወር የላከው 17 ሺህ 103 ነጥብ 2 ኩንታል እህል፣ ዘይት፣ አልሚ ምግብና ጥራጥሬ ሙሉ በሙሉ ደርሶ በመከፋፈል ላይ መሆኑን የየካቲት ወር ቀለብም በመጓጓዝና በመከፋፈል ላይ እንደሚገኝ ከዕርዳታ ፕሮግራሞች አፈጻጸምና ክትትል መምሪያ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህም ሌላ ኬር ኢትዮጵያ በድሬና በሞያሌ ወረዳዎች ለችግሩ ይበልጥ ለተጋለጡት ወገኖች 118 ሜትሪክ ቶን አልሚ ምግብ መድቦ እየተከፋፈለ ይገኛል፡፡ ድርጅቱ ድርቁ በእንስሳት ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ለመከላከል መንግሥት እያደረገ ያለውን ጥረት ለማገዝ 5 ሺህ የርቢ ላሞችን በመመገብ ሕይወታቸውን ለማትረፍ የሚያስችል 20 ሺህ እስር ድርቆሽ ሳር ገዝቶ በማከፋፈል ላይ ይገኛል፡፡

የውሃ አቅርቦትን በተመለከተም የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና የክልሉ አርብቶ አደር ኮሚሽን የላኳቸው 7 ቦቴዎች አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን፣ በወረዳዎች በኩልም 4 የጭነት መኪኖች በመከራየትና እያንዳንዳቸው 10 ሺህ ሊትር ውሃ የሚይዙ ስምንት የፕላስቲክ ጋኖች በመግዛት ውሃ መከፋፈሉንና በአጠቃላይ በ14 ቦቴዎች ለየወረዳዎቹ የውሃ አቅርቦት እየተከናወነ መሆኑን ከዋና አስተዳዳሪው ገለፃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በድርቁ በከፍተኛ ሁኔታ ከተጠቁት አካባቢዎች መካከል አንዱ የሆነውና በድሬ ወረዳ የሚገኘው የጎራይ ቀበሌ ሊቀመንበር አቶ አዮፍተ ጉዮ ድርቁ በእንስሳት ላይ ጉዳት እያስከተለ መሆኑን ገልዋል፡፡ የድሬ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሀላኬ ዋቆ ወረዳው 70 ሺህ ብር በመመደብ የውሃ አቅርቦት ችግሩን ለመቅረፍ እየጣረ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የሞያሌ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ጉዮ ዋሪዮ በበኩላቸው የክረምቱ ዝናብ ለሁለት ቀናት ብቻ በመጣሉ የእንስሳት ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑን ገልፀው ከፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የተላከው የዕርዳታ እህል መድረሱንና መከፋፈሉን ተናግረዋል፡፡

አሳሳቢ የሆነውን የውሃ ችግር ለመቅረፍ ወረዳው ከመጠባበቂያ በጀት 21 ሺህ ብር በመመደብ የተበላሸ የውሃ ቧንቧ መጠገኑን ፣ በ102 ሺህ ብር በጀት ለሕዝብ ውሀ የማደል ሥራ መስራቱን እና የተለያዩ ተያያዥነት ያላቸው የጥገና ሥራዎች መከናወናቸውን እንዲሁም የፕላስቲክ ውሀ ማጠራቀሚያ ጋኖች መገዛታቸውን ከወረዳው አደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ፅህፈት ቤትና ከመስተዳድር አካላት የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክልሉ አርብቶ አደር ኮሚሽን በውሀ አቅርቦቱ ረገድ የበኩሉን አስተዋጽዖ እያደረገ ሲሆን ፣ በጃጠን ኤምባሲ ድጋፍ ተቆፍረው በማሽን ብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡትን ስድስት የውሀ ጉድጓዶች ሥራ ለማስጀመር የጥገናው ሥራ በኦሮሚያ ውሀ ቢሮ እቅድ እንደተያዘለት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በቦረና ዞን ከተከሰተው የክረምትና የበልግ ዝናብ እጥረት ጋር በተያያዘ በህፃናት ላይ ያሳደረውን ተፅእኖ አጥንቶ የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ከነመፍትሂው የማሳየት ዓላማ ያለው የኒውትሪሽን ጥናት ከጥር ወር መጀመሪያ ሳምንት ጀምሮ ለ2 ሳምንታት በተልተሌ ፣ በሞያሌና በድሬ ወረዳዎች ተካሂዷል፡፡ በዚሁ መሠረትም እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው፡፡

በዚሁ ጥናት ላይ ከፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ፣ ከኦሮሚያ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንና ከኬር የተውጣጡ 23 ባለሙያዎች በሰባት ቡድኖች በመከፋፈል ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

## ኬር ቦረና በ21 ሚሊዮን ብር በጀት በአደጋ ተጋላጭነት ቅነሳ ፣ በምግብ ዋስትናና በጤና ክብካቤ ላይ ያተኮሩ ኘሮጀክቶችን እያካሄደ ነው

የኬር ኢትዮጵያ አካል የሆነው ኬር ቦረና የአርብቶ አደሩን የአደጋ ተጋላጭነት ለመቀነስ ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የጤና ክብካቤን ለማሻሻል የሚያግዙ ኘሮጀክቶችን በ21 ሚሊዮን ብር ያህል ወጪ በማካሄድ ላይ ነው::

የኬር ቦረና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሀላኬ ባንቴ ሰሞኑን ወደአካባቢው ተንቀሳቅሶ ከነበረው የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ እንደገለጹት ድርጅቱ የአርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር አኗኗር ማሻሻያ /Livelihood Enhancement for Pastoral and Agro Pastoral/ ኘሮጀክት እና የቦረና የአደጋ ተጋላጭነት ቅነሳ እንቅስቃሴ /Borana Vulnerability Reduction Initiative/ በመባል የሚታወቁ ሁለት ኘሮጀክቶችን ከኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን በስፋት ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል:: ከኦሮሚያ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን በተገኘ 6.5 ሚሊዮን ብር በጀት በኬር ቦረና አማካይነት ከኦክቶበር 2002 ጀምሮ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የቦረና የአደጋ ተጋላጭነት ቅነሳ እንቅስቃሴ ኘሮጀክት ቀደም ሲል በድርቅ ምክንያት ከብቶቻቸውን ላጡ አርብቶ አደሮች ድርቅን መቋቋም የሚችሉ እንደፍየል ያሉ እንስሳትን በነፃ ከማቅረቡም ባሻገር የመነሻ ካፒታል በመስጠት የሕብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ መርዳቱን የኬር ቦረና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሀላኬ አብራርተዋል::

በአብዛኛው ፍየል ንግድ ላይ ከተሰማሩት የሕብረት ሥራ ማህበራት መካከል አንዱ የሆነውና በድሬ ወረዳ የሚገኘው ማህበር በአንድ ዓመት ውስጥ 70 ሺህ ብር የተጣራ ትርፍ በማግኘት በሞዴልነት መመረጡን ከሥራ አስኪያጁ ማብራሪያ ለመረዳት ተችሏል:: ከዚህ በተጨማሪ በድሬና በያቤሎ ወረዳዎች የሚገኙ ሴቶችን በአስር የገቢ ማሳደጊያ ቡድኖች በማደራጀትና በሕብረት ሥራ ፅንስ ሀሳብ፣ በሂሳብ መዝገብ አያያዝና በንግድ ሥራ አመራር በማሰልጠን ለእያንዳንዱ ቡድን የ10 ሺህ ብር የመነሻ ካፒታል በመስጠት ድጋፍ እንደተደረገ ተገልጿል::

ኘሮጀክቱ በያበሎና ድሬ ወረዳዎች በሚገኙ የገበሬና የአርብቶ አደር ማህበራት ውስጥ ነዋሪ የሆኑ 14 ሺህ 513 ቤተሰቦችን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ሲሆን በክልል በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ መንግሥታዊ አካላትን በማሳተፍ የሚካሄድ መሆኑም ታውቋል::

እንደስራ አስኪያጁ ገለፃ የአሜሪካን ዓለም አቀፍ የልማት ተራድዖ ድርጅት **(USAID)** በመደበው የ14 ሚሊዮን 818 ሺህ 657 ብር በጀት በሶማሌ ክልል የሚገኙ ሁለት ዞኖችን ጨምሮ ለአምስት ዓመታት የሚካሄደው የአርብቶ አደርና የከፊል አርሶ አደርና አርብቶ አደር አኗኗር ማሻሻያ ኘሮጀክት በሰውና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በአቅም ግንባታ ረገድ ጉልህ አስተዋጽዖ እያበረከተ ነው::

ኘሮጀክቱ በያበሎና ድሬ ወረዳዎች በሚገኙ የገበሬና የአርብቶ አደር ማህበራት ውስጥ ነዋሪ የሆኑ 14 ሺህ 513 ቤተሰቦችን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ሲሆን በክልል በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ መንግሥታዊ አካላትን በማሳተፍ የሚካሄድ መሆኑም ታውቋል::

## በሶማሌ ክልልና ቦረና ዞን በተከሰተው ድርቅ ዙሪያ ከለጋሾችና መንግሥሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ውይይት ተካሄደ

በሶማሌ ክልልና በኦሮሚያ ቦረና ዞን በጥቅምትና ህዳር ወራት ይጠበቅ የነበረው ዝናብ በመጥፋቱ ሳቢያ ድርቁ ያስከተለውን ችግር ለመቋቋም በመንግሥት በኩል እየተወሰዱ ባሉ ጥረቶችና በቀጣይም መወሰድ በሚገባቸው የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፍላጎቶች ላይ ከተለያዩ የለጋሽ ሀገራት ተወካዮችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ውይይት



ችግሩን ለመቋቋም መንግሥት ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎችን በማቅረብ ፣ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ እንቅስቃሴውን የሚያስተባብሩ ግብረኃይሎችን በማቋቋም ከፍተኛ ጥረት በማከናወን ላይ ይገኛል::

ተካሄደ::

የካቲት 13 ቀን 1998 ዓ.ም በአመዝኤ የስብሰባ አዳራሽ በተደረገው በዚሁ የጋራ



ውይይት ላይ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሲሞን መቻለ ለውይይቱ ተሳታፊዎች እንደገለጹት በጥቅምትና ህዳር ወራት በቂ ዝናብ ባለመኖሩ በተለይም በሶማሌ ክልል በሊበን ፣ በአፍዴር ፣ በጎዴ ፣ በጅጅጋና በኦሮሚያ ቦረና ዞኖች ከፍተኛ የውሃ እና የግጦሽ እጥረት በመከሰት ላይ እንደሚገኝ ፣ የተከሰተው ችግር በእንስሶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን እና በህብረተሰቡም ላይ የምግብ እጥረት ማስከተሉን ገልፀዋል:: በአሁኑ ሰዓት የሚሰጡት የሜትሮሎጂ የመጀመሪያ ደረጃ የበልግ አዝማሚያ ትንበያዎች " ጉ" በመባል የሚታወቀው ዝናብ አስተማማኝ ባለመሆኑ የድርቁ ችግር በቀጣይ ወራት እንደሚባባስና ከዚሁ ጋርም የዕርዳታ ፍላጎቱ ከፍ ሊል እንደሚችል ያላቸውን ስጋት የገለፁት አቶ ሲሞን በዚህ ረገድ የሁኔታውን አሳሳቢነት በመረዳት ለሚያስፈልጉት የአስቸኳይ ጊዜ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች ለጋሽ ድርጅቶች ምላሽ እንደሚጠበቅባቸው አመልክተዋል::

ችግሩን ለመቋቋም መንግሥት ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎችን በማቅረብ ፣ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ እንቅስቃሴውን የሚያስተባብሩ ግብረኃይሎችን በማቋቋም ከፍተኛ ጥረት በማከናወን ላይ ይገኛል::

በምግብ አቅርቦት ረገድ በአሁኑ ሰዓት በመንግሥት እጅ ያለውን ከ230 ሺህ በላይ ሜትሪክ ቶን እህል ለተረጂዎች በአግባቡ ለማድረስ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ እንደሆነና በትራንስፖርት አቅርቦት ረገድ ያለውን ችግር ለማስወገድ የአውራ ጉዳና ባለሥልጣን የግል ትራንስፖርቱን ዘርፍ በማስተባበርና ከመከላከያ ሚኒስቴር ጋር ቅንጅት በመፍጠር የዕርዳታ አቅርቦቱ እንቅስቃሴ የሚፋጠንበትን ሁኔታ እያመቻቹ ነው ብለዋል::

በአሁኑ ሰዓት ችግሩ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ያለውን የምግብ ፣ የሰውና የእንስሳት ጤና ሁኔታ የሚከታተሉ ከአመዝኤ ፣ ከጤና ጥበቃና ግብርና ሚኒስቴር የተውጣጡ የባለሙያዎች ቡድኖች የተሰማሩ ሲሆን ፣ በፌዴራል ደረጃም የተቋቋሙት የጤና ፣ የውሃና የግብርና ግብረኃይሎች ከቡድኖቹ አስፈላጊውን መረጃ በማሰባሰብ በድርቁ ተጎጂ የሆኑ ተረጂዎችን ለመታደግና የእንስሳትን ጤና ለመንከባከብ በምግብ ፣ በመድኃኒትና በውሃ አቅርቦት ረገድ አቅም በፈቀደ መጠን በእጅ በሚገኘው የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ዋና ዳይሬክተሩ አብራርተዋል::

በአደጋው የተጎዱትን ወገኖች ለመታደግ የሚያስችል ዕርዳታ እንዲገኝ መንግሥት ከሚያደርገው ጥረት ጎን በመሰለፍ ክፍተት በታየባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ትኩረት በመስጠት እንደሚንቀሳቀሱ ለጋሾች አስታውቀዋል:: በስብሰባው ላይም ምግብ ነክ ላልሆኑ ፍላጎቶች 3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በስዊድን አምባሰደር በኩል ቃል ተገብቷል::

# ከሁለት ማዕከላዊ መጋዘናት ከ416 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተሠራጨ

ከመስከረም እስከ ጥር 1998 ዓ.ም ባሉት አምስት ወራት ውስጥ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ሥር ከሚገኙት የናዝሬትና የድሬደዋ ማዕከላዊ መጋዘናት በድምሩ 416 ሺህ 144.91 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ ተረጂዎች መሠራጨቱን ከሁለቱ ማዕከላዊ መጋዘናት የተገኙ መረጃዎች አመለከቱ፡፡

ከየማዕከላዊ መጋዘናቱ በተገኙ መረጃዎች መሠረት ሥርጭቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ፣ ሱማሌ ፣ አፋር ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደሁም ጋምቤላ ክልሎች ለሚገኙ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ነው፡፡ ከናዝሬት ማዕከላዊ መጋዘን የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው ከማዕከላዊ መጋዘኑ ከመስከረም እስከ ጥር 1998 ዓ.ም በድምሩ 272 ሺህ 257.91 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ የተሠራጨ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 127 ሺህ 416.12 ኩንታል ለኦሮሚያ ፣ 92 ሺህ 261.07 ኩንታል ለሱማሌ ፣ 40 ሺህ 578.01 ኩንታል ለአፋር ፣ 10 ሺህ 788.7 ኩንታል ለጋምቤላ እና 1 ሺህ 213.6 ኩንታል ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የተሠራጨ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ መልኩም ከድሬደዋ ማዕከላዊ መጋዘን ከመስከረም እስከ ታህሳስ 1998 ዓ.ም ባሉት አራት ወራት ውስጥ በድምሩ 143 ሺህ 887 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ በምሥራቅ ኦሮሚያና ሱማሌ ክልል ለሚገኙ ተረጂ ወገኖች ተሠራጭቷል፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ከተላከው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 78 ሺህ 286 ኩንታል ለሱማሌ ክልል ፣ ቀሪው 65 ሺህ 601 ኩንታል ደግሞ በኦሮሚያ ምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ ለሚገኙ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ፈላጊዎች የተሠራጨ ነው፡፡

ከሁለቱም ማዕከላዊ መጋዘናት የተሠራጨው አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ፣ የምግብ እህል የምግብ ዘይት ፣ አልሚ ምግብ ፣ ጥራጥ እና ብስኩትን ማካተቱ ታውቋል፡፡